የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ—ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 2
ADDIS ABABA 24th October, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
ለምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፩ሺ፱፻፳፱

## CONTENTS

Proclamation No. 290/2002
International Development Association Credit Agreement for Financing Food Security project Ratification Proclamation ...................... Page 1929

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፺/፲፱፻፺፭
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፷፰ ሚሊዮን ፩፻ሺ (ስድሣ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ጁን ፳፬ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺/፲፱፻፺፭» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## *PROCLAMATION NO. 290/2002*
## *A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION*

WHEREAS, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 68,100,000 (Sixty Eight Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights) for financing Food Security Project, was signed in Washington D.C., on the 24th day of June, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 24th day of October, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Food Security project Ratification Proclamation No. 290/2002."

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፳፬ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ ፮፻፵፮ ኢ.ት. የብድር ስምምነት ነው።

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፷፰ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ (ስድሣ ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆ[illegible]።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. Definition

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement Number 3646 ET signed in Washington D.C. on the 24th day of June, 2002 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 68,100,000 (Sixty Eight Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of October, 2002.

Done at Addis Ababa, this 24th day of October, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE